# እውነት ተናጋሪዋን አትመርጥም

ይኼን መልስ እንዳዘጋጅ የመጨረሻውን ግፊት የሠጠኝ፤ የዳኛቸው ቢያድግልኝ “በኢትዮጵያ ጉዳይ ይቅርታን ማን ይጠይቅ? ይቅርታስ ለምን?” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ፅሑፍ ነው። ይህን ፅሑፍ በማጠናቀር ላይ እያለሁ ሁለተኛ ፅሑፍ በማከታተል አበረከቱልን። የኑሮ ሩጫ ፋታ አልሠጥህ ብሎኝ ብዘገይም የጉዳዩ ድምቀት አይደበዝዝምና የበኩሌን ላካፍላችሁ። ሁለተኛ አከታትለው ያቀረቡት “ወደራሳችን እንመልከት፤ የተማርነው ከዕውቀት እንድንርቅ አምባገነንነትም እንድናከብር ነው” የሚለው ፅሑፋቸው ነው። ሁለተኛው ፅሑፋቸው ላይ ከሳቸው የተለዩ አመለካከት ሆነ ነጥብ እንደሌለኝ ጠቁሜ፤ ወደኋላ አንድ አስተያዬቴን አሰፍራለሁ። በመጀመሪያው ፅሑፋቸው ደግሞ ከሳቸው የተለዩ አመለካከት ስላለኝ ላካፍላችሁ ተነሳሁ።

እንደ ዳኛቸው ቢያድግልኝ ፅሑፍ በግልፅ ተሰምሮበት አይቅረብ እንጅ ፅንሰ ሃሳቡ በድህረ ገፆችና በየቡና ተርቲመኞች ሪጋ ሲንሸራሸር ዉሎ አድሯል። <u>የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ለተከተለው ምስቅልቅል ተጠያቂ ማድረጉ!</u> ዳኛቸው ቢያድግልኝ በግልፅ አስምረው በማቅረባቸው አመሰግናቸዋለሁ። የሃሳብ ልዩነት በጎና ይበል ሊባል የሚገባው ድንቅ ባሕል ነው። በግልፅ ከመዉጣት ይልቅ በሥር ለሥር እያለኸለኹ የሚሠረነቁ አባባሎች የመራኸነት ኪነት እንጅ የመወያያ ነጥብነት ይዘት የላቸውም። “ዱባና ቅል ለየቅል” ነውና።

በተጨማሪ ዳኛቸው ለፅሑፋቸው መንደርደሪያ ላቀረቧቸው ሁለት ወጣት ኢትዮጵያዊያን እኔም የዳኛቸውን ሃቀኛ ምስጋና እጋራቸዋለሁ። ከዚህም በላይ ዳኛቸው፤ “ጀግንነት በዕውቀት ካልተገዛ መልሶ ሊያጠፋ የሚችል መሆኑን . . . ” ብለው ያሰፈሩት ትልቅ ትምህርት ነው።

አንባቢያን እዚህ ላይ ሐቅንና አስተያዬትን ለይቼ ላስቀምጥ። በወቅቱ የተካሄደውን ክስተት፤ ማለትም በተማሪው እንቅስቃሴ ወቅት፤ ተማሪው ስላነሣቸው ጥያቄዎች፣ ስላነገባቸው መፈክሮችና፣ ስለከፈለው መስዋዕትነት ልዩነት የለንም። የተከሰተውን ሃቅ በየትኛውምና በማንኛውም ዓይነት መነፅር ብንመለከተው፤ አንድና አንድ ነው። ያልነበረና የሌለ አይጠፋም፤ የነበረና ያለ አይፈጠርም። ልዩነት የተፈጠረው ትንተና በሚሰጥበት ወቅት ነው። ማለትም አሁን ወደኋላ ዞረን፣ ጊዜ በለገሠን ተመክሮ ደልብተን፣ ይኼ፤ ያንን ወለደ፤ እያልን፤ ማዛመድ ስንጀምር ነው። በዚህ ደግሞ ከተሄደ፤ ለኢሕአፓ ተግባር የተማሪውን እንቅስቃሴ፣ ለደርግ ፍጅት ኢሕአፓን፣ ለወያኔ ሀገር ማጥፋት ደርግን እንወነጅልና፣ ወያኔን ነፃ ማውጣቱ ስላሰጋኝ ነው።

እንግዲህ ወደ ልዩነታችን ከመጓዜ በፊት፤ በዚሁ ድህረ ገፅና በሌሎችም እንዲሁ ቀደም ሲል፤ ማለትም በየካቲት ወር ፳፻ ዓ. ም. የትውልድ አከፋፈልን በድፍረት በመተንበይ፤ የኛን ትውልድ አስመልክቶ፤ ያቀረብኩትን ፅሑፍ ለአድማጭ ማስገንዘብ እወዳለሁ።

## <u>የኛ ትውልድ</u>

*አንፃራዊ ዕይታ፤ ላለንበት አጣብቂኝ የፖለቲካ ሁኔታ*
*ከመፍትሔ ፍለጋ አኳያ፤ ገፀ ባህሪያችንን ለመጠቆምና፤ ውይይት ለመክፈት፤*
*ከይኑጋል በላቸው - የካቲት ፳፻ ዓ. ም.*

በዚሁ ፅሑፍ አንድን ትውልድ ከሌላው ትውልድ የበለጠ ወይንም ያነሰ ብሎ ከመፈረጅ በፊት፤ ያ ትውልድ ያፈጠጠበትን ታሪካዊ ኃላፊነት ለይቶ መረዳት፤ በተለይም “ወርቃማው ትውልድ” በማለት የኛኑ ትውልድ አንቆለባብሶ ማስቀመጡ እንዳልተዋጠልኝ በማመልከት፤ ከጀግነቱና ከወርቃማነቱ አንፃር ይኼንኑ ጀግንነትና ወርቃማነት ለተጠየቀበት ምክንያት መንስዔው የዚሁ ትውልድ አባላት መሆናችን በግልፅ አስፍሬአለሁ።

የዳኛቸው ቢያድግልኝን ፅሑፍ መንስዔ በማድረግ ይኼንን ላዘጋጅ የገፋፋኝ፤ ይህ የተማሪውን እንቅስቃሴ የጀምላ ምቱ፤ ከላይ ከጠቀስኩት ስጋቴ በተጨማሪ፤ ለወደፊት ሁለታችንም ለምንሻው ፍቅርና ኅብረት ዕንቅፋትነቱ ጎልቶ ስለታየኝ ነው።

የተማሪዎችን እንቅስቃሴ ነጥሎ፤ በወቅቱና ታሪክ ባቀረበለት ጥያቄ ሚዛን ማነፃፀሩን ትተን፤ ከዚያ በተከተለው ሂደት ክስተት መለካት፤ ትክክል አይደለም።

በአሥራ ዘጠኝ መቶ ሃምሣዎቹ ሁለተኛ ግማሽና በአሥራ ዘጠኝ መቶ ስድሣዎቹ የመጀመሪያ ግማሽ ላይ ለነበረው ተማሪ ታሪክ ያቀረበለት የድርሻው ሙግት ምን ነበር? ለዚህስ ሙግት ተማሪው፤ በተለይ ኃላፊነቱን የተረዳው ክፍል ምን መልስ አቀረበ? የተማሪው እንቅስቃሴ የሚታዬው፤ በዚህና በዚህ ብቻ ነው። የምንማረው ምን ነበር? የምንማረውስ የት ለመድረስ ነበር? እነኚህን በመመለስ እጀምራለሁ።

እኔ በዚህ የተማሪዉ እንቅስቃሴ ሲደራ ከመካከሉ አካባቢ ነበር የደረስኩ። በተደጋጋሚ ከዚያ ወዲህ ለተከሠተው ጥፋት ውርጅብኝ በሚደረደርበት ይኼው የተማሪ እንቅስቃሴ ተሣታፊ ነበርኩ። ከወዲሁ ለአንባቢ፤ ንቁ ተሣታፊና አሁንም እንደያኔው የምኮራበት ተግባር መሆኑን ላመላክት እፈልጋለሁ። መሪ አልነበርኩም። በአንፃሩ ደግሞ አንድን ግለሰብ ወይንም ብዙኀኑን ተከትዬ የነጎድኩ አልነበርኩም። ስለአመንኩበትና ለጠየቀው መስዋዕትነት ስለተዘጋጀሁ ተሣትፌአለሁ። ለዚህ ነው ንቁ ተሣታፊ ነበርኩ ብዬ ያሠመርኩበት። በዚህም በወቅቱ ከነበሩት ተሣታፊዎችም ሆነ መሪዎች ያላነሰ ተጠያቂነት አለብኝ። በፀጋ የምቀበለው።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ በሁለተኛው ፅሑፋቸው የተማርነውና የተዘጋጀነው ለምን እንደነበር በደንብ ግልፅ አድርገውታል። የማስቀምጠው አስተያዬት፤ በዘመኑ የነበረው የተማሪ ቁጥር፤ በሀገራችን ለትምህርት አቅሙ ከደረሰው ወጣት አንፃር እጅግ አነስተኛ መሆኑን ነው። እናም ይኼ ቁንጽል ክፍል የሀገሪቱንና የኢትዮጵያዊያንን የዘመኑን ትውልድ ወካይ አለመሆን ላሠምርበት እወዳለሁ። ከዚህም አልፎ ተርፎ፤ ሁሉንም ባንድ ላይ ማላተሙ፤ ሀገሪቱን የአንድ ገፀ-ባህሪ ብቻ ማምረቻ እንደሆነች ያመላክታልና መቀበሉ ይቸግረኛል። ዳኛቸው ቢያድግልኝ በሁለተኛው ፅሑፋቸው የተማርነው ፍርሃትን ነው በማለት ጥቅልል አድርገው አስቀምጠውታል። እኔ ደግሞ ከፍርሃትም አጥብቤ አስቀምጠዋለሁ። ከጠዋት ሰልፉ አንስቶ እስከ ፀሐይ ግባት ድረስ፤ ንጉሠ ነገሥቱን ለማመሥገን፣ ልዩ ፍጡርና፣ የአምላክ ተቀቢነታቸውን ለማድነቅና፣ የኛን ትቢያነት ለመገንዘብ፣ በአራት ግድግዳ ተከብበን ወጣቶች ተሠገሠግን። ይህ ነበር የትምህርታችን መሠረቱ።

ከዚሁ ምኞታቸው ባሻገር ግን ስለሌሎች ሀገሮች እና የአገዛዝ ፍልስፍናቸው ጭላንጭል ለመገንዘብ ዕድል፤ ቀዳዳ ተፈጠረልን። በተለይም ውጭ ሀገር ወጥተው ለመማር ዕድል ያገኙት በሀገር ከነበርነው የበለጠ፤ በዚህ ሰዓት፤ የቀሪው ዓለምን ዕድገትና ግሥጋሤ ከመገንዘብ ባሻገር፤ የአፍሪካ ሀገሮችን የነፃነት ነፋስ ሲነቀንቃቸው ተመለከቱ። የከበበን ግን፤ ትምህርት በሀገሪቱ በሙሉ ሳይስፋፋ ለተወሠኑ ከባቢዎችና የኅብረተሰቡ ክፍሎች አድልዖ የነበረበት፣ ጢሰኞች በችግር ሲንገላቱ የሚያርሱበትን መሬት፣ የለፉበትን ምርትና፣ አልፎ ተርፎ ጉልበታቸውንና ሕይወታቸውን የለገሷቸው ባላባቶች የሚንደላቀቁባት ነበር። ድርቅ፣ ረሀብ፣ እና በሺታ የሀገሪቱ ከተመኞች ሆነው ሳል፤ በትልቅ የጉራ የውስጥ ጋቢ እና የላይ ካባ ተሸፍነዋል። የሀገራችን ኋላ ቀርነት በድንቁርና ትምክህተኝነት ተከደዋል።

ያኔ ተማሪው ከማንም በፊት ቀድሞ መሬቱ፤ ለሚለፋበት አራሽ ሊሰጠው ይገባል አለ። ትምህርት ለደሃውም ልጅ ይድረሰው አለ። ዳኛቸው ቢያድግልኝ ፤ “. . . በመጀመሪያ ከዕውቀት ጋር ጠብ እንደጫሩና ተማሪውን ከዕውቀት፤ ምሁሩን ከውይይት፤ እንደነጠሉትና

EthioLion.Com

ወደፍርሃትና ሽብር እንደጨመሩት ዛሬን ድረስ የተገነዘቡት አይመስልም።” በማለት በዚያ ወቅት እንደሳቸው አባባል ተማሪውን ያሳሳቱ፤ ከዚያ ወዲህ ደግሞ በፖለቲካ ድርጅት በመሪነት ያሉ ያሏቸውን ወንጅለዋቸዋል። ምንም እንኳ ይህ ዉንጀላ የማይፈርጀኝ ነኝ ብዬ መመፃደቅ ብችልም፤ ዕምነቴ ከነሡው ጋር ይለትመኛልና፤ መልስ እሠጣለሁ። ለመሆኑ ከየትኛው ትምህርት ነው የተነጠለው? ተማሪው መሆኑ ነው። የወቅቱ። ሀለት እግር አለኝ ብሎ ሁለት ዛፍ መውጣት አይቻልም። ይልቁንም በዚሁ ወቅት፤ ሠልጥነው የአባቶቻቸውን መሥሪያ ቤት እንዲወርሱና በደሃ ላያ እንዲቧርቁ የተንከባከቧቸው ልጆቻቸው፤ አሻፈረኝ ብለው ከኛ ከድሆች በመወገን መሥዋዕት የሆኑትን ሳስታውስ፤ ይህ ትግል ምን ያህል የከበረና ጥልቅ ሰብዕና የተመላበት እንደነበር እገነዘባለሁ። ጥላሁን ይግዛውን፣ ማርታ መብራቱን፣ መስፍን ሀብቱን፣ ያመላክቷል።

አንባቢ የኔን ሙግት ልብ ብለው ይከተሉ። ለኢሕአፓ፣ ለመኢሶን፣ እና ለየነፃ አውጭ ድርጅቶች ልማት ሆነ ጥፋት በታሪክ የቀደማቸው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ተጠያቂ አይደለም። የተማሪው እንቅስቃሴ የሚጠየቀው በተከሰተበት ወቅት ባነሣቸው ጥያቄዎች፣ ባነገባቸው መፈክሮች፣ እና በከፈላቸው መስዋዕትነት ነው።

ዳኛቸው ቢያግልኝ በፅሑፋቸው መካከል፤ “አሁን እንደሚታወቀው ማንኛውም ግለሰብ ወደ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ሲገባ ገና በሺህ ዘጠኝ መቶ ሀምሳዎቹ ውስጥ የኤርትራን መገንጠል አምኖ ለዚህም የአቅሙን እንደሚያደርግ ቃል ገብቶ ነበር መሬት ለአራሹን መዘመር የሚጀምረው።” በማለት አዲስ ታሪክ ፅፈዋል። አዲስ ታሪክ ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለም። ቀደም አድርጌ እንዳነጠብኩት አስተያየትን መሥጠት አንድ ነገር ነው። በዚህ ላይ ደግሞ አስተያየቶቹ እንደየግለሰቡ የተለያየ ዕምነትና ግንዛቤ የተለያዩ ይሆናሉ። ያለፈን ክስተት ቀይሮ ማቅረብ ደግሞ ሲሆን . . . ሌላ፤ በለዘበ አባባል ደግሞ ፈጠራ እለዋለሁ። ፈጠራ፤ ምክንያቱም፤ እንደገና - ያልነበረና የሌለ አይጠፋም፤ የነበረና ያለ አይፈጠርም። አዲስ ታሪክ መፍጠር መሆኑ ነው። እንኳንስ በሺህ ዘጠኝ መቶ ሀምሳዎቹ ቀርቶ በሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሣ ሁለትና ሶስት የኤርትራን መገንጠል ትቶ፤ በኤርትራ የመገንጠል ንቅናቄ መኖሩን የሚያውቀው ክፍል ከመቶው ሁለት እጁ ቢሆን ይገርመኛል። ይህ ማለት በወቅቱ ከነበርነው ሶስት ሺህ ተማሪዎች መካከል ከስድሣ ያልበለጡ ማለት ነው። ይኼንን ቁጥር በለጋስነት ያበዛሁት ዳኛቸውን ላስደስት፣ ውይይቱን መልክ ላለማሣጣት ከጅዬ ነው። እነኚህ ደግሞ ከሁሉ ቀድመው ትምርት ለደሀው እንዲደርስ፣ ጢሰኛው የራሱ መሬት እንዲያገኝ ይታሰሩ፣ ይገረፉ የነበሩ ናቸው። እኒህን የሕዝብ አገልጋዮች፤ አብዛኞቹ ሕይወታቸውን የለገሱ፤ የድብቅ ጉዳይ ይዘው ነበር ብሎ መወንጀል፤ አንድም የወቅቱን የፖለቲካ ሂደት አለመረዳት፣ አለያ ደግሞ አሁን በተያዘው ሁሉን ነገር በተማሪው ላይ እንዘፍዝፈው ለሚለው ዜማ ጨብጨብ ሲሆን፣ ሲከፋ ደግሞ በወቅቱ ለነበረው የበሰበሰ መንግሥት ጥብቅናና መልሶ ለማምጣት የሚደረግ ከንቱ ድካም አቀንቃኝነት ነው። የተማሪው ትግል ታሪካዊ ሚናውን አሚጠ፤ ደርግ የሕዝቡን ሥልጣን ነጥቆ፣ ተቃዋሚዎቹ በየቦታው ባቆጠቆጡበት ወቅት ኤርትራ ከሞላ ጎደል በነበረው መንግሥት ቁጥጥር ሥር ነበረች። የወቅቱ የተማሪ ትግል ምዕራፉ ተዘጋ። ያጨበጨቡት የፖለቲካ ፖርቲዎችና ለሀገር ተቆርቋሪዎች በወቅቱ የኤርትራ ጉዳይ የፖለቲካ መፍትሄ ይሠጠው ዘንድ አጨብጭቧል። የደርግን ደርጋማነት ተጠቅሞ፤ የኤርትራ ወጣቶችን በጭፍን ጥላቻ አስሮ፤ ለግል ጠባብና አረመኔያዊ የፖለቲካ ጥማቱ፤ ኢሳያስ አፈወርቂ፤ በቡችላው በመለስ ዜናዊ አገልጋይነትና፣ በየዋህ ለጋ የትግራይ ወጣቶች አማካይነት፤ ከደርግና ከወያኔ በከፋ ሁኔታ ከቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል በበለጠ ኤርትራዊያን ወጣቶችንና ሰላማዊ ሕዝብ ፈጅቶ ኤርትራን ገነጠለ። ተማሪው አይጠየቅበትም። ተማሪዉ አሁንም ያለውን መንግሥት በ፲፱፻፺፫ እና በ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. ዐቅሉን እንዳሳጣው፤ ታሪካዊ ተልዕኮውን ተወጥቷል፣ እየተወጣ ነው፣ ይወጣልም።

አሁን ለጎደለንና ላለንበት አጣብቂኝ ውጥንቅጥ የፖለቲካ አረንቋ ተጠያቂዎቹ እኛው የወቅቱ ባለቤቶች ነን። እኔ፣ ዳኛቸው ቢያድግልኝ፣ ባሁን ሰዓት በተቃዋሚው ጎራ የተሠለፉ ድርጅቶች በሙሉ፤ ትናንት ተማሪዎች የነበርን በመሆናችን ሳይሆን፤ የዛሬ ባለቤቶች በመሆናችን ተጠያቂዎች ነን። የወያኔዉ ቡድን የሚችለውን ጥፋት በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ ነው። ፀረ ኢትዮጵያ የሆኑት "ነፃ አውጭ" ነን ባዮች በተመሣሣይ ግብር በሠፊዉ ተሠማርተዋል።

ኢትዮጵያዊነትን ያነገቡ ድርጅቶች፤ በተለይም መሪዎቻቸው በጣም ያሣዝናሉ። ወቅቱ የሚጠይቀውን፤ በሃቅ ግልፅ ሆኖ ለሀገር ሕልውና የግል ጥቅምን በማስገዛት፤ እንደያኔዎቹ ተማሪዎች ሙሉ ዕምነት ኖሯቸው፣ ለሕዝቡ በመቆም፡ በድፍረት ለዕውነት ተነሥተው፣ እንደ "መሬት ለአራሹ"፤ "ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያዊያን"፣ እንደ "ትምህርት ለደሀው"፤ "ሥልጣን ለሕዝብ"፣ በማለት ከጎንደር እስከ አለማያ፣ ከዩኒቨርሲቲ ተማሪ እስከ ሁለተኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአንድነት እንደተነሱ ሁሉ፤ በአንድነት፤ በአንድ ጣምራ አለመሠባሠባቸው፤ ፍዳችንን አብዝቶታል። መወነጃጀሉ ቀላል ነው። ወቀሳው እንደሁ ለያንዳንዳችን ዕቅፍ ደርሶ ይተርፋል። ዞሮ ዞሮ ግን፤ ማታ የት ይተኛል ነው፡? አልኩ ለማለት የሚደረጉ የትብብር ጥሪዎች ደጅ አይወጡም። ወቅቱ የሚጠይቀው ግልፅነትን ነው። ወቅቱ የሚጠይቀው ድፍረትን ነው። ወቅቱ የሚጠይቀው አርቆ አስተዋይነትን ነው። ወቅቱ የሚጠይቀው የሕዝብ አገልጋይነትን ነው። ይህ ደግሞ የሺህ ዘጠኝ መቶ ሀምሳዎቹና የሺህ ዘጠኝ መቶ ስድሳዎቹ ተማሪዎች አኩሪ ባህሪ ነበር።

EthioLion.Com